# ክ ፍ ል - ሦ ስ ት

## ለክርስቲያኖች የተሰጡ ተስፋዎች

በክፍል ሁለት ያየናቸው ተስፋዎች በዚህ ክፍልም ይቀጥላሉ። ጌታን በተቀበልን ጊዜ በሕይወታችን ውስጥ የተፈጸሙት ነገሮችና ከጌታ ጋር በክርስትና ሕይወት ውስጥ ስንመላለስ የሚፈጸሙት ተስፋዎች ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው ተስፋዎች ጋር ይወራረሳሉ። ዛሬ በሕይወትህ እየተፈጸሙ ያሉ ተስፋዎች ምን እንደሆኑ አጽንኦት ሰጥተህ እንድታያቸው በማሰብ በአንዳንዶቹ ነጥቦች ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል፤

### 1. የዓለም ጨው ሆነሃል

"እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም።" (ማቴ. 5፡13)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተጠቀሰው ጨው የሚከተሉትን ተግባራት ይወክላል፤

1.1 ጨው ጣዕም ይሰጣል። እግዚአብሔር እኛን ሲያድነን 1. ጣዕም (ትርጉም) ላልነበረው ሕይወታችን ጣዕምና ትርጉም ይሰጠዋል። 2. በሕይወታቸው ጣዕም ለሌላቸው ጣዕምን እንዲሰጥ ጸጋውን በሕይወታቸው ውስጥ አስቀመጠ። ስለዚህ ተልዕኮአችን በቃሉ እንደተገለጸው "ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁል ጊዜ በጨው እንደ ተቀመመ በጸጋ ይሁን፤" ይላል። (ቆላ. 4፡6)

1.2 ጨው ምግብን በተለይም ሥጋን እንዳይበላሽ ያደርጋል። የክርስቲያኖችም ተልዕኮ ለዓለም ከዚህ የተለየ አይደለም። በኃጢአት በተበላሸ ዓለም ውስጥ

የሚኖሩ የእግዚአብሔር ልጆች የራሳቸውን ሕይወት ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ሕይወት በኃጢአት ከመበላሸት ይጠብቃሉ።

1.3 ጨው ቃል ኪዳን የሚጸናበት መሣሪያ ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የጨው ቃል ኪዳን አይለወጥም። «የእስራኤል ልጆች ከተቀደሰው ነገር ሁሉ አንሥተው ለእግዚአብሔር ያቀረቡትን ለአንተ ከአንተም ጋር ለወንዶችና ለሴቶች ልጆችህ ድርሻ እንዲሆን ለዘላለም ሰጥቼሃለሁ፤ በእግዚአብሔር ፊት ለአንተ ከአንተም ጋር ለዘርህ የጨው ቃል ኪዳን ለዘላለም ነው።» (ዘኁ. 18፡19) እግዚአብሔር በወንጌል ስብከት የሚያምኑትን ሁሉ ለማዳን የሰጠው ቃል ኪዳን ለክርስቲያኖች ነው። እንግዲህ ሕይወት ጣዕም እንዲሰጥ ወደ ጥፋት የምታመራውን ዓለም በወንጌል ተስፋ ለማዳን ከጌታ የተላክን ምስክሮች ነን። ከክርስቲያኖች ሌላ እግዚአብሔር ለዓለም ሌላ መልእክተኛ አያስነሣም። «እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ተናገረ፤ እኔም ይህን ብቻ ሰማሁ ኃይል የእግዚአብሔር ነው።» (መዝ. 61፡11)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የጨው ባሕርያት ምን እንደሆኑ በዝርዝር አመልክት?

◆ ______________________________

◆ ______________________________

◆ ______________________________

◆ ______________________________

◆ ______________________________

2. ጨው ለምን ይጠቅማል?

◆ ______________________________

◆ ______________________________

◆ ______________________________

◆ ______________________________

◆ ______________________________

3. የዓለም ጨው ናችሁ ለምን ተባልን?

◆ ______________________________

◆ ______________________________

◆ ______________________________

______________________________

## 2. በክርስቶስ ከአሸናፊዎች በላይ ሆነሃል

“በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።” (ሮሜ 8፥37)

“ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።” (1ቆሮ. 15፥57)

“ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ ለሚያዞረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ ምሥጋና ይሁን።” (2ቆሮ. 2፥14)

2.1 ክርስቶስ ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት አንድ ጊዜ ለዘላለም በሚጸና ቃል ኪዳን መንፈሳዊውን ጦርነት አሸንፏል። ይህን አሸናፊነት ገና ተዋግተን የምናገኘው ሳይሆን፤ የተፈጸመ ስለሆነ በእምነት ተቀብለን የምንኖርበት ድል ነው። እንግዲህ ከአሸናፊዎች በላይ ያደረገን እኛ ሳንዋጋ ክርስቶስ ባደረገው ድል በሥልጣን መኖር ስለምንችል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በድፍረት “ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።” ያለው ለዚህ ነው (ፊልጵ. 4፥13)።

2.2 ሥልጣንና ኃይል ለክርስቶስ ስለ ተሰጥቷል። በመታዘዙም በመስቀሉ ሞትና ትንሣኤ ሁሉንም ስለ አሸነፈ፤ እግዚአብሔር አብ ከሁሉ በላይ የሆነውን ስምና ሥልጣን ሰጠው ሁሉም ለእርሱ ጌትነት ይገዛል። (ፊል. 2፥9–10፤ ኤፌ. 1፥22) ተመልከት። ስለዚህም የክርስቶስ ኢየሱስ ስም ከሁሉም በላይ ነው። “ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።” (ፊል. 2፥9–10) ስለዚህ በዚህ ስም የጸሎት መልስ ይገኛል።

2.2.1 በስሙ ደህንነት ይገኛል፦ “መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።” (ሐዋ. 4፥12)

2.2.2 በስሙ የኃጢአት ይቅርታ አለ።

2.2.3 በስሙ ፈውስ አለ፤ “ጴጥሮስ ግን፦ ብርና ወርቅ የለኝም፣ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው።” (ሐዋ. 3፥6)

2.2.4 በስሙ አጋንንት ይወጣሉ፤ “ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፣ እባቦችን ይይዛሉ፤ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።” (ማር. 16፥17)

2.2.5 የጌታ ስም ሥልጣን ሁሉ ያለው ስም ነው። “ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ አላቸው፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፤” (ማቴ. 28፥18)

2.2.6 ለክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉም ተገዝቶለታል። “ሁሉም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው።” (ኤፌ. 1፥22)

2.2.7 ክርስቶስን ከሞት ያስነሣው መንፈስ በእኛ ውስጥ ይኖራል። “የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንደሆነ በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤“ (ኤፌ. 1፥17–19)

እነዚህንና እነዚህ የመሳሰሉት እውነቶች ናቸው በክርስቶስ ውስጥ ያለነውን ሰዎች አሸናፊዎች ብቻ ሳይሆን ከአሸናፊዎችም በላይ እንድንሆን የረዱን። በእግዚአብሔር ውስጥ እስከ አለን ድረስ ጦርነቱ የእኛ ሳይሆን የእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርም ደግሞ ማሸነፍን እንጂ መሸነፍን አያውቅም። ጦርነት የተለማመደው ንጉሥ ዳዊትም ደጋግሞ የሰማው ስለ እግዚአብሔር ኃይል መሆኑን ሲመሰክር፦ "እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ተናገረ፦ እኔም ይህን ብቻ ሰማሁ ኃይል የእግዚአብሔር ነው፤" አለ። (መዝ. 61፡11)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ከአሸናፊዎች በላይ መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

- ◆ ____
- ◆ ____
- ◆ ____
- ◆ ____
- ◆ ____

2. አሸናፊ ሕይወት ከዕለታዊ ኑሮ ጋር እንዴት ይዛመዳል?

- ◆ ____
- ◆ ____
- ◆ ____
- ◆ ____
- ◆ ____

## 3. የክርስቶስ መልእክተኛ ሆነሃል

"ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፤ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።" (2ቆሮ. 5፡18-20)

የክርስቶስ መልእክተኞች መሆናችንን ካረጋገጥን ልንዘነጋቸው የማይገቡ ብዙ እውነቶች አሉ፤

1. መልእክቱን የምናደርስበት ሁኔታና ስጦታዎች ይለያዩ እንጂ በቃልም ሆነ በሕይወት የምናስተላልፈው የማስታረቅ መልክት አንድ ነው። የምንሰብከው ወይም የምንመሰክረው ወንጌል ክርስቶስ ሞቶ ተቀብሮ በሦስተኛው ቀን እንደ ተነሣ ነው። ስለዚህ የትንሣኤ መልክተኞች ነን። ይህም በመሆኑ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" ያለው። (ገላ. 1፡8)

2. ሁላችን የክርስቶስ መልእክተኞች ብንሆንም እንኳ ስጦታዎቻችን የተለያዩ ናቸው። የስጦታችን መለያየት የማስታረቅ ቃል ከመሸከም ነፃ አያደርገንም። ይህም ስለሆነ በስጦታችን ምክንያት የበታችነትም ሆነ የበላይነት ስሜት ሳይሰማን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምስክሮች መሆን ይገባናል።

3. መልእክተኛ የራሱ መልዕክት የለውም፤ የሚያስተላልፈው የላኪውን መልዕክት ነው።

4. በእኛ በኩል የሚማልደው ጌታ ስለሆነ ለመንፈስ ቅዱስ ድምፅ ልባችን ክፍት መሆን ይገባዋል።

5. የማስታረቅ አገልግሎት የከበረ አገልግሎት መሆኑን በማስተዋል ታማኝ የክርስቶስ አምባሳደር መሆን አስፈላጊ ነው።

6. ጥሪያችን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅና ማስተዋወቅ ብቻ ሳይሆን እንደ ዮሐንስ መጥምቁ ደግሞ ሰዎችን እርስ በእርስ ማስታረቅ እንደሆነም ያለመዘንጋት ተገቢ ነው። ሉቃ. 1፡17 ተመልከት።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. መልእክተኛ መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. የመልእክተኛ ኃላፊነት ምንን ያጠቃልላል?

- 
- 
- 

# 4. መልካም እረኛ አለህ

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝም የለም።" (መዝ. 22፡1) "መልካም እረኛ እኔ ነኝ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።" (ዮሐ. 10፡11) "እኔ ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ አስመስጋቸውማለሁ፣ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።" (ሕዝ. 34፡15)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ለእኛ የሰጠ መልካም እረኛ ነው ስንል፤

1. ሊጠብቀን፦ "በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፤ ይገባልም ይወጣል መሰማሪያም ያገኛል።" (ዮሐ. 10፡9)

2. ሊመግበን፦ "ከአሕዛብም ዘንድ አወጣቸዋለሁ ከአገሮችም አሰበስባቸዋለሁ፤ ወደ ገዛ አገራቸውም አመጣቸዋለሁ፤ በእስራኤልም ተራሮች ላይ በፈሳሾችም አጠገብ በምድርም ላይ ሰዎች በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ አሰማራቸዋለሁ። በመልካም መሰማሪያ አሰማራቸዋለሁ ጎረኖአቸውም በረጅሞቹ በእስራኤል ተራሮች ላይ ይሆናል፤ በዚያ በመልካም ጎረኖ ውስጥ ይመሰጋሉ፤ በእስራኤል ተራሮች ላይ በለመለመ ማሰማሪያ ይሰማራሉ። እኔ

ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ አስመስጋቸውማለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።" (ሕዝ. 34፡13-14)

3. ሊመራን፦ "መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፤ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፤ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል።" (ኢሳ. 40፡11) ደግሞ መዝ. 22 ተመልከት።

4. ሊሸከመን፦ እርሱን ለመከተል እንኳን አቅም ካነሰን መልካሙ እረኛችን አንሥቶ በጫንቃው እንደሚሸከመን ቃል ኪዳን ገብቶልናል። "በግብጻውያን ያደረግሁትን በንሥርም ክንፍ እንደ ተሸከምኋችሁ፤ ወደ እኔም እንደ አመጣኋችሁ አይታችኋል።" (ዘጸ. 19፡4)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የእረኛ ኃላፊነት ምንድን ያጠቃልላል?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

2. የእረኛ መኖር ለምን ይጠቅማል?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

## 5. የማይተኛ ጠባቂ አለህ

"እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም፤ የሚጠብቅህ አይተኛም። እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም። እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፤ እግዚአብሔርም በቀኝ እጅህ በኩል ይጋርድሃል። ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም ጨረቃም በሌሊት። እግዚአብሔር ከክፉ ይጠብቅሃል፤ ነፍስህንም

ይጠብቃታል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል።” (መዝ. 120፡3–8)

የእግዚአብሔር ጥበቃ ሁሉንም ዓይነት ጥበቃን ያጠቃልላል። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን የጥበቃ ቃል ኪዳኖች እንመልከት፦

1. ደህንነታችን በእርሱ ዋስትና ያለውና የተጠበቀ ነው፤ “እኔም የዘላለምን ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ ለዘላለምም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፤ ከአባቴም እጅ ሊነጠቃቸው ማንም አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን።” (ዮሐ. 10፡28–29)

2. እንዳንሰናከል ይጠብቀናል፤ “እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም የሚጠብቅህም አይተኛም።” (መዝ. 120፡3)

3. ከጠላታችን ይጠብቀናል፤ “በላባዎቹ ይጋርድሃል፤ በክንፉ በታች ትተማመናለህ እውነት እንደ ጋሻ ይከብብሃል። ከሌሊት ግርማ በቀን ከሚበር ፍላጻ፤ በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር፤ ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም። በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ፤ ወደ አንተ ግን አይቀርብም።” (መዝ. 90፡4–7)

4. ከመከራ ይጠብቀናል፤ “መከራዬን አይተሃልና፤ ነፍሴንም ከጭንቀት አድነሃታልና በምሕረትህ ደስ ይለኛል ሐሴትም አደርጋለሁ።” (መዝ. 30፡7)

5. ከጠላት ወጥመድ ይጠብቀናል፤ “እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንሃልና።” (መዝ. 90፡3) እንዲሁም መዝ. 124፡7 ተመልከት።

6. ከአደጋ ይጠብቀናል፤ “በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር፤ ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም።” (መዝ. 90፡6)

7. ሥጋችንን፤ ነፍሳችንንና መንፈሳችን ከኃጢአትና ከነቀፋ ሁሉ ይጠብቃል። 1ተሰ. 5፡23 ተመልከት።

በእግዚአብሔር ጥበቃ ውስጥ ስንመላለስ ሌላው እጅግ የሚያረካው ነገር እንዴት እንደሚጠብቀን ማወቁ ስለሆነ የሚከተሉትን ነጥቦች በጥሞና እንመልከት።

1. እንደ ዓይኑ ብሌን ይጠብቀናል። "የሚነካችሁ የዓይኑን ብሌን የሚነካ ነውና።" (ዘካ. 2፡8)

2. ያለ እንቅልፍ ይጠብቀናል። "እነሆ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም፤ አያንቀላፋምም።" (መዝ. 120፡4)

3. በጥላው ከለላ ሥር ይጠብቀናል። "በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል።" (መዝ. 90፡1)

4. በእጁ ከለላ ውስጥ ይጠብቀናል። "ሰማያትን እዘረጋ ዘንድ ምድርንም እመሠርት ዘንድ ጽዮንንም፡- አንቺ ሕዝቤ ነሽ እል ዘንድ ቃሌን በአፍህ አድርጌአለሁ፤ በእጄም ጥላ ጋርጄሃለሁ።" (ኢሳ. 51፡16)

5. በመላእክቶቹ ይጠብቀናል። "በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና።" (መዝ. 90፡11)

6. በስሙ ይጠብቀናል። "ቅዱስ አባት ሆይ፤ እነዚህ የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው።" (ዮሐ. 17፡11)

7. በዓይኖቹ ይጠብቀናል። "ከእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ ዓይኖቼ በምድር ምእመናን ላይ ናቸው፤ በቀና መንገድ የሚሄድ እርሱ ያገለግለኛል።" (መዝ. 100፡6) እንዲሁም ኤር. 24፡6 ተመልከት።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ጥበቃ ምንን ይጨምራል?

◆

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

2. የማይተኛ ጠባቂ ስንል ምን ማለታችን ነው?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

## 6. እግዚአብሔር መሪ ሆኖልሃል

"ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፤ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል። የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፤ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፤ ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም፤ የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና።" (ዮሐ. 10፥3-4)

እግዚአብሔር ልጆቹን ወዴት እንደሚመራቸው የሚያውቅ አዳኝ፣ እረኛና አጽናኝ ነው። እግዚአብሔር ወዴትና እንዴት ይመራኛል? ለሚለው ጥያቄ የሚከተሉትን እውነታዎች በማስተዋል ብትመረምርና በእምነት ብትቀበል መልስ ይሆንሃል።

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር የሚመራህ ወዴት ነው?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

2. እግዚአብሔር እንዴት ይመራኛል ብለህ ታስባለህ?

- ◆

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________

# እግዚአብሔር የሚመራን ወዴት ነው?

1. እግዚአብሔር ወደ ሕይወት ይመራል። “ለዓለምና ለዘላለም ይህ አምላካችን ነው፤ እርሱም ለዘላለም ይመራናል።” (መዝ. 47፡14)
“እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ሕይወት ይመራል።” (ምሳ. 19፡23)

2. ሙላት ወዳለው ሕይወት ይመራል። “...እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።” (ዮሐ. 10፡10)

3. ወደ በጎ ፈቃዱ ይመራል። “ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ ብትል ጆሮችህ በኋላህ፦ መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ የሚለውን ቃል ይሰማሉ።” (ኢሳ. 30፡21)

4. ወደ እውነት ሁሉ ይመራል። “ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል።” (ዮሐ. 16፡13)

5. ወደ ለመለመ መስክ ይመራል። “በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።” (መዝ. 22፡2)

6. ወደሚያረካ ሕይወት ይመራል። “የሚራራላቸውም ይምራቸዋልና፤ በውኃም ምንጮች መካከል ይነዳቸዋልና አይራቡም፤ አይጠሙም፤ ትኩሳት ወይም ፀሐይ አይጎዳቸውም።” (ኢሳ. 49፡10)

7. ወደ ድል ሕይወት ይመራል። "ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንግሥቱ ለሚያዞረን በእኛም በየሥፍራው ሁሉ የዕውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ ምስጋና ይሁን።" (2ቆሮ. 2፡14)

8. ወደ ጥበብ ይመራል። "የጥበብን መንገድ አስተማርሁህ።" (ምሳ. 4፡11)

9. ወደ ትክክለኛ መንገድ ይመራል። "በቀናች ጎዳና መራሁህ።" (ምሳ. 4፡11)

10. ወደ እግዚአብሔር ቅድስና ይመራል። "ብርሃንህና እውነትህን ላክ፤ እነርሱ ይምሩኝ፣ ወደ ቅድስናህም ተራራና ወደ ማደሪያህ ይውሰዱኝ።" (መዝ. 42፡3)

## እግዚአብሔር የሚመራን እንዴት ነው?

እግዚአብሔር እንዴት ይመራል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚከተለውን በጥንቃቄ ማጥናት ይጠቅማል?

1. ሁልጊዜ ይመራናል። "እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይመራሃል፤ ነፍስህንም በመልካም ነገር ያጠግባል አጥንትህንም ያጠናል..." (ኢሳ. 58፡11)

2. በመንፈሱ ይመራል። "በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።" (ሮሜ 8፡14)

3. በምክሩ ይመራል። "በአንተ ምክር መራኸኝ ከክብር ጋር ተቀበልኸኝ።" (መዝ. 72፡24)

4. በእጁ ይመራል። "በዚያ እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝህም ትይዘኛለች።" (መዝ. 138፡10)

5. እስከ መጨረሻ ይመራል። "ለዓለምና ለዘላለም ይህ አምላካችን ነው፤ እርሱም ለዘላለም ይመራናል።" "በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና..." (መዝ. 47፡14፤ ፊል. 1፡6)

6. በእውነቱ ይመራል። "አንተ የመድኃኒቴ አምላክ ነህና በእውነትህ ምራኝ፤ አስተምረኝም።" (መዝ. 24፡5)

7. በቃሉ ይመራል። "ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው።" (መዝ. 118፡105)

8. በኃይሉ ይመራል። "በቸርነትህ የተቤዠሃቸው ሕዝብህን መራህ፤ በኃይልህ ወደ ቅዱስ ማደሪያህ አገባሃቸው።" (ዘፀ. 15፡13)

9. በብርሃኑ ይመራል። "ብርሃንህንና እውነትህን ላክ እነርሱ ይምሩኝ፤" (መዝ. 42፡3)

10. በፍቅሩ እያባበለ ይመራል። "ስለዚህ እነሆ፤ አባብላታለሁ ወደ ምድረ በዳም አመጣታለሁ፤ ለልቡዋም እናገራለሁ።" (ሆሴ. 2፡16)

## 7. ጸሎትህ የሚሰማና የሚመለስልህ ሆነሃል

"በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።" (ዮሐ. 15፡7)

"እኔም እላችኋለሁ ለምኑ ይሰጣችሁማል፣ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያውንም አንኳኩ ይከፈትላችሁማል።" (ሉቃ. 11፡9)

"የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፤ የሚፈልገውም ያገኛልና፤ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።" (ማቴ. 7፡8)

«ይጠራኛል እመልስለትማለሁ፤ በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ፤ አድነዋለሁ፤ አከብረውማለሁ።» (መዝ. 90፡15)

"እንዲህም ይሆናል ሳይጠሩ እመልስላቸዋለሁ፤ ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ።" (ኢሳ. 65፡24)

ጸሎታችንን ስለ መስማቱና ስለመመለሱ እግዚአብሔር የጸና ቃል ኪዳን ገብቶልናል። የሚከተሉትን የተስፋ ቃል ኪዳኖች መርምረህ በቃሉ መሠረት ብትጸልይ እግዚአብሔር ጸሎትህን ይመልሳል። እግዚአብሔር የሚመልሳቸው የጸሎት ዓይነቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፦

1. የንስሐ ጸሎት፦ "በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፤ ፊቴንም ቢፈልጉ፤ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፤ ኃጢያታቸውንም ይቅር እላለሁ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።" (2ዜና 7፡14)

2. የእምነት ጸሎት፦ "ስለዚህ እላችኋለሁ የጸለያችሁትን፤ የለመናችሁትንም እንዳገኛችሁ እመኑ ይሆንላችሁማል።" (ማር. 11፡24)

3. በክርስቶስ ኢየሱስ ስም የምንጸልየው ጸሎት፦ "ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።" (ዮሐ. 14፡14)

4. የስምምነት ጸሎት፦ "ደግሞ እላችኋለሁ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል።" (ማቴ. 18፡19)

5. በክርስቶስ ውስጥ ሆነን የምንጸልየው ጸሎት፦ "በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።" ( ዮሐ. 15፡7)

6. በቃሉ መሠረት የምንጸልየው ጸሎት፦ "በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።" (ዮሐ. 15፡7)

7. በመንፈስ ቅዱስ የምንጸልየው ጸሎት፦ “መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል።” (ሮሜ 8፡26)

8. እንደ ፈቃዱ የምንጸልየው ጸሎት፦ “በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል። የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን።” (1ዮሐ. 5፡14-15)

9. ለአብ ክብር የሚሆነው ጸሎት፦ “በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል። ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል።” (ዮሐ. 15፡7-8)

10. ፈቃዱን የምናደርግ ከሆነ፦ “ትእዛዙንም የምንጠብቅና በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን የምናደርግ ስለ ሆንን የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን።” (1ዮሐ. 3፡22)

## <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. ጸሎት ምንድነው?

♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________

2. ለምንድነው የምንጸልየው?

♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________

3. እንዴት ነው መጸለይ ያለብን?

♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________

- ___
- ___

4. እግዚአብሔር እንደሚሰማህ ከምታውቅባቸው መንገዶች ጥቂቶቹን ዘርዝር?

- ___
- ___
- ___
- ___
- ___

## 8. ጌታ ድምፁን ያሰማሃል

ጌታ እንደሚሰማኝ በማወቅ ለጸሎት በእምነት ወደፊቱ ብቀርብ ልጠቀም እንደምችል አምናለሁ።

"የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፤ ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና።" (ዮሐ. 10፡4)

"ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፊቀቅ ብትል ጆሮችህ በኋላህ፦ መንገዱ ይህች ናት በእርስዋ ሂድ የሚለውን ቃል ይሰማሉ።" (ኢሳ. 30፡፡21)

"እርሱም ገና ሲናገር እነሆ፤ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው እነሆም ከደመናው፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።" (ማቴ. 17፡5)

የልጆቹን ድምፅ ለመስማትና የእርሱ ለሆኑት ድምፁን ለማሰማት ጌታ ቃል ገብቶልናል ነው። ድምፁን ለመስማት ደግሞ በቅድስና ሕይወት ከጌታ ጋር መመላለስና ቃሉን ማንበብ፤ ልብን እልከኛ አለማድረግ፤ ለመታዘዝ ፈቃደኛ መሆንንና እንዲናገረን መፍቀድ ይጠበቅብናል። የሚከተሉትን ተስፋዎች የሰጠውም ለዚሁ ነው፦

1. ክርስቶስ ለበጎቹ ድምፁን ያሰማል። "ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፤ የራሱም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።" (ዮሐ. 10፡3)

2. አብ በክርስቶስ ለልጆቹ ድምፁን ያሰማል። "መጨረሻም ለእኛ ተናገረን፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢያታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።" (ዕብ. 1፡3)

3. በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለልጆቹ ድምፁን ያሰማል። "ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፦ ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት፥ አባቶቻችሁ እኔን የፈተኑበት የመረመሩበትም አርባ ዓመትም ሥራዬን ያዩበት በምድረ በዳ በፈተና ቀን በማስመረር እንደ ሆነ፥ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ። ስለዚህ ያን ትውልድ ተቆጥቼ፦ ዘወትር በልባቸው ይስታሉ መንገዴን ግን አላወቁም አልሁ፤" (ዕብ. 3፡7–10)

4. በቃሉ ድምፁን ያሰማል። "ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።" (ማቴ. 7፡24)

5. በቤተ ክርስቲያን አማካይነት ድምፁን ያሰማል። "መንፈሱና ሙሽራይቱም፦ ና ይላሉ። የሚሰማም፦ ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፤ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።" (ራዕ. 22፡17)

## 9. ከፍቅሩ የሚለይህ የለም

"ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስደት፤ ወይስ ራብ፤ ወይስ ራቁትነት፤ ወይስ ፍርሃት፤ ወይስ ሰይፍ ነውን? ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፤ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው። በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። ሞት ቢሆን፤ ሕይወትም ቢሆን፤ መላዕክትም ቢሆኑ፤ ግዛትም ቢሆን፤ ያለው ቢሆን፤ የሚመጣውም ቢሆን፤ ኃይላትም ቢሆኑ፤ ከፍታም ቢሆን፤ ዝቅታም ቢሆን፤ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን

ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።” (ሮሜ 8፡35–39)

ከጌታ ፍቅር ሊለየን የሚችል ምንም ነገር እንደሌለ እላይ የተጠቀሰው የጌታ ቃል ማረጋገጫ ነው። “ምንም የለም” የሚለው ቃል የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

1. ከውጭ የሚመጣው መከራና ስደት፤
2. የወደፊቱ ቢሆን ወይም የአሁን የምናልፍበት ፈተና፤
3. የኑሮ ትግል እና ውጣ ውረድ፣ ማጣት፣ ማግኘት፣ ወ.ዘ.ተ
4. ከውስጣችን ከሚነሱ የሥጋ ፈተናዎች፤
5. ለሕይወት አስፈሪ የሆኑ ነገሮች፤ ሞትም እንኳን ቢሆን፤
6. ከሰይጣንና ከመላዕክቶቹ ከሚመጡ ፈተናዎች።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. በጌታ ፍቅር ለመኖር ምን ያስፈልጋል ትላለህ?

- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______

2. የጌታ ፍቅር ጠባያት ምንድናቸው?

- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______

## 10. ሁሉን ለመልካም ያደርግልሃል

“እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።” (ሮሜ 8፡28) “ለእናንተ የማስባትን አሳብ

አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።" (ኤር. 29፥11)

በጌታ ውስጥ ሆነን እንደ ፈቃዱ በቃሉ ምሪትና በመንፈሱ ኃይል የምንኖር ከሆነ ያለ እርሱ ፈቃድ በሕይወታችን ውስጥ የሚሆን ነገር አይኖርም። ከመወለዳችን በፊት እርሱ ሁሉንም በመዝገቡ ጽፎታልና። "ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ የተፈጠሩ ቀኖቼን ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ።" (መዝ. 138፥16)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ሁሉም ለበጎ ነው ማለት ምን ማለት ነው?

◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___

2. ሁሉም ለበጎ የሚሆነው ለእነማን ይመስልሃል?

◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___

3. ሁሉም ለበጎ ሊሆን የማይችለው ለእነማን ነው? ለምን?

◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___

# 11. የጌታ ደስታ ያንተ ነው

"ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ። ገርነታችሁም ለሰው ሁሉ ይታወቅ። ጌታ ቅርብ ነው።" (ፊል.4፥4–5)

“ጻድቃን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ ለቅድስናውም መታሰቢያ አመስግኑ።” (መዝ. 96፡12)

“እግዚአብሔር የተቤዣቸው ይመለሳሉ ወደ ጽዮንም ይመጣሉ የዘላለምም ደስታ በራሳቸው ላይ ይሆናል ደስታንና ተድላን ያገኛሉ፤ ኀዘንና ልቅሶም ይሸሻል።” (ኢሳ. 51፡11)

“እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በመድኃኒቴ አምላክ ሐሴት አደርጋለሁ።” (ዕምባ. 3፡18)

## <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. የእግዚአብሔር ደስታ ጠባያት ምን ያካትታሉ?

- ♦ ___
- ♦ ___
- ♦ ___
- ♦ ___
- ♦ ___

2. በጌታ ደስታ ለመኖር ምን ያስፈልጋል?

- ♦ ___
- ♦ ___
- ♦ ___
- ♦ ___
- ♦ ___

3. የጌታ ደስታ ከአገልግሎት ጋር ምን ግንኙነት አለው?

- ♦ ___
- ♦ ___
- ♦ ___
- ♦ ___
- ♦ ___

# 12. የመንፈስ ነጻነት ተሰጥቶሃል

“ጌታ ግን መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ።” (2ቆሮ. 3፡17)

"እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።" (ዮሐ. 8፥36)

ጌታ ያዳነን ለእርሱ በነጻነት እንድንኖር ነው። ነጻነታችንን የሚገፍ ማንኛውም ነገር ከጌታ ስላልሆነ በሕይወታችንና በኑሮአችን ሊሠለጥን አይገባውም። "በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።" (ገላ. 5፥1) ስለ ነጻነታችን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ቢኖር ከጌታ የተሰጠንን መንፈሳዊ ነጻነት ለከፋት መሸፈኛ እንዳንጠቀምበት ብቻ ነው። "ወንድሞች ሆይ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያት አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በእርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።" (ገላ. 5፥13) እንዲሁም 1ጴጥ. 2፥16 ተመልከት።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የመንፈስ ነጻነት ምንን ያጠቃልላል?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. የመንፈስ ነጻነትና የሥጋ አርነት አብረው ሊሠሩ ይችላሉን?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

3. እንዴት?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

4. ለምን?

- ______
- ______

♦
♦
♦

## 13. ጌታ ከጭንቀት ነጻ አድርጎሃል

"በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።" (ፊል. 4፥6)

"እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያጩንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።" (1ጴጥ. 5፥7)

የእግዚአብሔር ቃል እንዳንጨነቅ ብቻ ሳይሆን ከሚያስጨንቀን ሃሳብና ሸክም ነጻ ሆነን እንድንኖር ጭምር ያስተምረናል። ከጭንቀት ነጻ ሆነን ለመኖር የሚከተሉትን በሕይወታችን መለማመድ ይጠበቅብናል፤

1. በጸሎት ሕይወት መኖር፤

2. በምስጋና መመላለስ፤

3. መንገዳችንን ለእርሱ አደራ መስጠት፤

4. የሚያስጨንቀንን በእርሱ ላይ መጣል፤ እንዲሁም

5. እርሱ ለእኛ የሚያስበው የተሻለ እንደ ሆነ በእምነት ተቀብሎ መኖር ናቸው።

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. ከጭንቀት ነጻ መሆን ማለት ለኑሮ ያለ ማሰብ ማለት ነውን?

♦
♦
♦
♦
♦

2. በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት አመልክት?

♦

- 
- 
- 
- 

## 14. ከአቅምህ በላይ እንድትፈተን አይፈቅድም

"ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፤ ትታገሱም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።" (1ቆሮ. 10:13)

እግዚአብሔር ልጆቹን በክፉ አይፈትንም። "ማንም ሲፈተን በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንምና እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም።" (ያዕ. 1:13) ከሥጋ፤ ከዓለምና ከሰይጣን ፈተና በሚመጣበት ጊዜ ከአቅማችን በላይ እንድንፈተን አይፈቅድም። በድካማችንና በፈተናችንም ውስጥ ይረዳናል፤ ያስብልናል፤ ወደ ዙፋኑ ፊት ስንቀርብ አስፈላጊውን ጸጋ ይሰጠናል። "ከኃጢያት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፤ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም። እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።" (ዕብ. 4:15–16)

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. የፈተና ምንጮች ምንድን ናቸው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. እግዚአብሔር ፈተናን ይፈቅዳልን?

- 

♦
♦
♦
♦

3. ከፈቀደ ለምን?

♦
♦
♦
♦
♦

4. ፈተና ጥቅም አለው ወይ?

♦
♦

## 15. ከፈተና ሁሉ የምታመልጥበትን መውጫ ሁሉ ሰጥቶሃል

"ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው። ትታገሱም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።" (1ቆሮ. 10፥13)

"ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን፤ በደለኞችንም ይልቁንም በርኩስ ምኞት የሥጋን ፍትወት እየተከተሉ የሚመላለሱትን ጌትነትንም የሚንቁትን እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዴት እንዲጠብቅ ያውቃል።" (2ጴጥ. 2፥9)

ፈተና በሚመጣበት ጊዜ እግዚአብሔር ለልጆቹ ይከላከልላቸዋል። ብቻቸውንም አይተዋቸውም። መዝ. 36፥33 ተመልከት። ይህ ማለት ሊመጣ ካለው ፈተና ሁሉ ይጠብቃቸዋል ማለት ነው። "የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ።" (ራዕ. 3፥10) ፈተናም ከደረሰ በኋላ የምንወጣበትን መንገድ በማዘጋጀት ድልን ይሰጠናል። ይህም ማለት፦

1. አብሮን በመሆን እንዳንንዳ ይከላከልልናል። "ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" (ማቴ. 28፥21)

1.1 የእሳትን ኃይል ያጠፋል። (ዳን. 3፥26–27 ተመልከት)

1.2 ሰንሰለታቸውን ይቆርጣል። (ዳን. 3፥25 ፤ ሐዋ. 16፥26)

2. አብሮ በመሆን ያበረታታናል። "ሁሉም ተውኝ እንጂ ይህንም አይቁጠርባቸው፣ ዳሩ ግን የስብከቱ ሥራ በእኔ እንዲፈጸም አሕዛብም ሁሉ እንዲሰሙት፥ ጌታ በእኔ አጠገብ ቆሞ አበረታኝ፥ ከአንበሳ አፍም ዳንሁ።" (2ጢሞ. 4፥17)

3. መልአኩን ይልካል። "በፊቱ ቅንነት ተገኝቶብኛልና በአንተም ፊት ደግሞ፥ ንጉሥ ሆይ፤ አልበደልኩምና አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ፤ እነርሱም አልጎዱኝም አለው።" (ዳን፥ 6፥22)

4. የብረት መዝጊያውን ይከፍታል። "የመጀሪያውንና የሁለተኛውንም ዘብ አልፈው ወደ ከተማ ወደሚያወጣው ወደ ብረቱ መዝጊያ ደረሱ እርሱም አውቆ ተከፈተላቸው፤ ወጥተውም አንዲት ስላች አለፉ ወዲያውም መልአኩ ከእርሱ ተለየ።" (ሐዋ. 12፥10)

5. ባሕሩን ይከፍላል። "ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ እግዚአብሔርም ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አስወገደው፤ ባሕሩንም አደረቀው፤ ውኃውም ተከፈለ።" (ዘፀ. 14፥21)

6. ማዕበሉን ጸጥ ያደርጋል። "እርሱም እናንተ እምነት የጎደላችሁ ስለምን ትፈራላችሁ? አላቸው፤ ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ፤ ታላቅ ጸጥታም ሆነ።" (ማቴ. 8፥26)

7. ከዓለት ውኃን ያፈልቃል። "ሙሴም እጁን ዘርግቶ ድንጋዩን ሁለት ጊዜ በበትሩ መታው፤ ብዙም ውኃ ወጣ፤ ማኅበሩም ከብቶቻቸውም ጠጡ።" (ዘኁ. 20፥11)

8. እንደ ጎልያድ ታላቅ የሆነውን ፈተና እንድታሸንፍ እንደ ዳዊት ኃይልን ይሰጥሃል። "ዳዊትም እጁን ወደ ኮሮጆው አግብቶ አንድ ድንጋይ ወሰደ ወነጨፈም፤ ፍልስጤማዊውንም ግንባሩን መታው፤ ድንጋዩም በግንባሩ ተቀረቀረ፣ እርሱም በምድር ላይ በፊቱ ተደፋ።" (1ሳሙ. 17፥49)

9. በፈተና ውስጥ ድልን ይሰጥሃል። እንደ ኢያሪኮ ግንብ በፊትህ የቆመውን እንቅፋት ያፈርስልሃል። "ሕዝቡም ጮኹ፤ ካህናቱም ቀንደ መለከት ነፉ ሕዝቡም የቀንደ መለከቱን ድምፅ በሰሙ ጊዜ ታላቅ ጩኸት ጮኹ፤ ቅጥሩም ወደቀ ሕዝቡም ሁሉ እያንዳንዱ አቅንቶ ወደ ፊቱ ወደ ከተማይቱ ወጣ፤ ከተማይቱንም ወሰዱ።" (ኢያ. 6፥20)

10. በጠላት ላይ ድልን ይሰጣል። "ሰልፉ ለእግዚአብሔር ነውና፤ እናንተንም በእጃችን አሳልፎ ይሰጣል።" (1ሳሙ. 17፥47)

11. በፈተና ውስጥ ስንሆን ከጉዳት ይጠብቀናል። "በውኃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም፤ በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፤ ነበልባሉም አይፈጅህም።" (ኢሳ. 43፥2)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. መውጫ የሌለው ፈተና አጋጥሞህ ያውቃል?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

2. የፈተና መውጫው መንገድ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ነውን?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

3. የመውጫ መንገድና የእግዚአብሔር ጊዜ ግንኙነታቸው ምንድነው?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

## 16. ጌታ የሚያስፈልግህን ሁሉ ይሰጥሃል

"አምላኬ እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል።" (ፊል. 4፥19)

"ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም።" (ሮሜ. 8፥32)

"ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።" (ማቴ. 6፥33)

ዓለምና ሞላዋን በሙሉ ጌታ የፈጠረው ለራሱ ክብርና ለልጆቹ ጥቅም ነው። ስለዚህ ጌታ ልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን ምንም ነገር አይከለክላቸውም። ይህን በረከት በሙላት ለመቀበል የሚያስፈልጉን ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፦

1. የጌታን መንግሥት ማስቀደም፦ ኑሮአችን ጌታን የሚያስከብር ከሆነና ለፈቃዱ የምንገዛ ከሆንን ለኑሮ የሚያስፈልገንን ሁሉ እርሱ ይሰጠናል።

2. ለእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ በፍቅርና በእምነት የምንሰጥ ከሆነ ጌታ የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሰጠናል።

3. የእግዚአብሔር የሆነውን ለእግዚአብሔር የምንሰጥ ከሆነ እግዚአብሔር ይባርከናል። (ሚል. 3፡7–12)

4. በልግስና የምንሰጥ ከሆነ ጌታ አብልጦ ይባርከናል። "ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፤ የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል።" (ሉቃ. 6፡38)

5. የሚያስፈልገንን ነገር በእምነት የምንጠይቅ ከሆነ እርሱ ይሰጠናል። (ሉቃ. 11፡10)

6. የእግዚአብሔርን ተስፋ በትክክል መረዳት፡- የእግዚአብሔር ቃል የሚነግረን የሚያስፈልገንን እንደሚሰጠን ነው እንጂ የምንፈልገውን ሁሉ እንደሚሰጠን አይደለም።

7. እግዚአብሔር ለልጆቹ በዘመናት ሁሉ ታማኝ ነው። እግዚአብሔር በዘመናት ውስጥ ለልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን እንደ ሰጣቸው ቃሉ ይመሰክራል። (መዝ. 106 የእስራኤላውያን ታሪክ ጥሩ ምሳሌ ነው)

8. የእግዚአብሔር ዓላማ እንድንባረክና የበረከቱ ማስተላለፊያ እንድንሆን ነው። (ዘፍ. 12፡1–2 ተመልከት።)

9. ለእግዚአብሔር መታዘዝ አስፈላጊ ነው። «እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ፤ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤» (ኢሳ. 1፡19)

10. የልባችን ደስታ በእርሱ ከሆነ የልባችንን መሻት ይሰጠናል። (መዝ. 36፡4 ተመልከት።)

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. በሰው ፍላጎትና በአስፈላጊ ነገሮች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

◆
◆
◆
◆
◆

2. የተሰጠንን ተግባራዊ ለማድረግ ምን ይጠበቅብናል?

◆
◆
◆
◆
◆

## 17. በኃይልና በድፍረት እንድትኖር ተጠርተሃል

"እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃትን መንፈስ አልሰጠንምና።" (1ጢሞ. 1፡7)

መጽሐፍ ቅዱስ ፍርሃትን አስወግደን በድፍረት መኖር እንደሚገባን ብዙ መመሪያዎች ከመስጠቱም በላይ "አትፍራ" የሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜያት ተጠቅሷል። በድፍረት እንድንመላለስ የሚያስችለን የጌታ መንፈስ ኃይል፤ ጌታ ከእኛ ጋር መሆኑ፤ በእኛ ውስጥ ያለው በዓለም ካለው መብለጡ፤ ለእኛ የተሠጠው የጌታ ቃል ኪዳን የማይለወጥ መሆኑና እንዲሁም እርሱ ለእኛ ያለው ፍቅርና እኛም ለእርሱ ያለን ፍቅር ከሚጠቀሱት ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው። "ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፤ ፍርሃት ቅጣት አለውና የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።" (1ዮሐ. 4፡18)

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. መንፈሳዊ ድፍረት ምንድነው?

◆
◆
◆
◆
◆

2. ያለ ፍርሃት መኖር ማለትስ ምን ማለት ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

3. ፍርሃት ራሱ ምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

4. ፍርሃት በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ከሚያደርሳቸው ጉዳቶች ምካከል ጥቂቱን ዘርዝር?

- 
- 
- 
- 
- 

5. ያለ ፍርሃት ለመኖር ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

- 
- 
- 
- 
- 

## 18. የተሳካ ሕይወት ተሰጥቶሃል

"ነገር ግን ጽና፥ እጅግ በርታ፤ ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፥ አድርገውም፤ በምትሄድበት ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል።" (ኢያ. 1፡7)

"ስለዚህ በምታደርጉት ሁሉ ትከናወኑ ዘንድ የዚህን ቃል ኪዳን ቃሎች ጠብቁ አድርጉም።" (ዘዳ. 29፡9)

እንደ ፈቃዱ የምንኖር ከሆነ ጌታ የእኛችንን ሥራ፤ ቤታችንን፤ ኑሮአችንን ሁሉ ለስሙ ክብር ይባርካል። ከእነዚሁ መካከል ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል፦

18.1 በሁሉም ነገር መባረክ፦ "ሁሉን አብዝቶ ስለ ሰጠህ አምላክህን እግዚአብሔርን ..." (ዘዳ. 28፥47) "የተሰወረውን የአሸዋውን መዝገብ የባሕሩንም ባለጠግነት ይጠግባሉና አሕዛብንም ወደ ተራራው ይጠራሉ፤" (ዘዳ. 33፥19)

18.2 በሰላምና በእውነት መባረክ፦ "...የሰላምና የእውነት ብዛት እገልጥላቸዋለሁ።" (ኤር. 33፥6)

18.3 ያለው ይበዛለታል፦ "ላለው ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤" (ማቴ. 13፥12)

18.4 በእግዚአብሔር ስጦታ መባረክ፦ "የእግዚአብሔርም ሰው፦ ከዚህ አብልጦ ይሰጥህ ዘንድ እግዚአብሔር ይችላል ብሎ መለሰለት።" (2ዜና. 25:9)

18.5 በጸጋው መባረክ፦ "ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ በብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።" (ሮሜ 5፥17)

18.6 በብዙ ደስታ መባረክ፦ "የደስታቸው ብዛት ...የልግስናቸውን ባለጠግነት አብዝቶአል፤" (2ቆሮ. 8፥2)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር የፈጠረህ ለመከናወን ከሆነ ይህን በየዕለቱ ለመለማመድ ምን እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል ብለህ ታምናለህ?

- ________________________________
- ________________________________
- ________________________________

♦ ____________________

♦ ____________________

2. የመከናወን መለኪያው ምን እንደ ሆነ አስበህ ታውቃለህ? ሃሳብህን በዝርዝር አስፍረው።

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

## 19. ጌታ ፈዋሽህ ሆኖአል

"በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸው ብዙዎች ወደ እርሱ አመጡ በነቢዩ በኢሳያስ፦ እርሱም ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንን ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ፤ መናፍስትን በቃሉ አወጣ። የታመሙትን ሁሉ ፈወሰ።" (ማቴ. 8፡17)

"ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት።" (ያዕ. 5፡14)

እግዚአብሔር ፈጣሪ፣ አዳኝና ፈዋሽ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። ለጤንነት ወይም ለፈውስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባውን ቃል ኪዳን እንመልከት፦

1. የግብጻውያንን በሽታ በሕዝቡ ላይ አያመጣም፤ "አንተ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ፤ በፊቱም የሚበጀውን ብታደርግ፤ ትዕዛዙንም ብታደምጥ፤ ሥርዓቱንም ሁሉ ብትጠብቅ፤ በግብጻውያን ላይ ያመጣሁትን በሽታ አላደርስብህም፤ እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝና አለ።" (ዘፀ. 15፡26)

2. እግዚአብሔር የሕዝቡ ፈዋሽ ነው፤ "ኃጢያትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፤ ደዌሽን ሁሉ የሚፈውስ፤" (መዝ. 102፡3)

3. እግዚአብሔር የተሰበረውን መንፈስ ይፈውሳል፤ "ልባቸው የቆሰሉትን ይፈውሳል፤ ሕመማቸውን ይጠግናል።" (መዝ. 146፡3)

4. ክርስቶስ ሕመማችንን ተሸክሟል፤ "እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደህንነታችን ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።" (ኢሳ. 53፡5) "ለኃጢያት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢያታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ።" (1ጴጥ. 2፡24)

5. ክርስቶስ ሥጋን ለብሶ በመጣ ጊዜ ሰዎችን ይፈውስ ነበር። ስለዚህም ዛሬም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያንን ሥራ አላቋረጠም። አራቱን ወንጌላት አጥና።

6. በሽተኞችን የመፈወስ ጸጋ ለአማኞች ተሰጥቷል። "አሥራ ሁለቱንም ሐዋርያት በአንድነት ወደ እርሱ ጠርቶ በአጋንንት ሁሉ ላይ ደዌንም ይፈውሱ ዘንድ ኃይልና ሥልጣን ሰጣቸው፤ የእግዚአብሔርንም መንግሥት እንዲሰብኩ ድውዮችንም እንዲፈውሱ ላካቸው።" (ሉቃ. 9፡1–2)

7. ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በክርስቶስ ስም ይፈውሱ ነበር። (የሐዋርያት ሥራን አጥና።)

8. መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልዩ የመፈስ ስጦታን የሚሰጣቸው ሰዎች አሉ። (1ቆሮ. 12፡9 ተመልከት።)

9. የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ዘይት ቀብተው ለታመሙ ሰዎች እንዲጸልዩ ታዘዋል። (ያዕ. 5፡14 ተመልከት።)

እነዚህ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ሃሳብ ጤንነት እንደ ሆነና በሽታ ከእርሱ እንዳልሆነ ያሳያሉ። ስለዚህ በጌታ ውስጥ ስንኖር የመንፈስና የነፍስ ብቻ ሳይሆን የሥጋም ፈውስ አለን። "ወዳጅ ሆይ፤ ነፍስህ እንደሚከናወን በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ።" (3ዮሐ. 1፡2)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ስለ ጌታ ፈዋሽነት በርግጥኝንት ታምናለህን?

- ________________
- ________________
- ________________
- ________________
- ________________

2. ጌታ ፈውስን የሚሰጠው ለነማን ይመስልሃል?

- ________________
- ________________
- ________________
- ________________
- ________________

3. ፈውሱ ለሁሉም ነው ብለህ ታስባለህን?

- ________________
- ________________
- ________________
- ________________
- ________________

4. ፈውሱን ለመቀበል ምን ዝግጅት ያስፈልጋል?

- ________________
- ________________
- ________________
- ________________
- ________________

## 20. ለፍሬያማ አገልግሎት ተሹመሃል

"እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፤ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ።" (ዮሐ. 15፡16)

በጌታ ውስጥ የተባረከው ሕይወታችን ብቻ ሳይሆን አገልግሎታችንም ጭምር ነው። ስለዚህ የተሾምነው ሠላሳና ስድሳ እና መቶ ፍሬ እንድናፈራ ነው። (ማር. 4፡20 ተመልከት።) ከፍሬያማ አገልግሎት ጋር የተሰጡን መመሪያዎች፡-

20.1 ሹመቱ ከጌታ ስለ ሆነ ቸል እንዳንል።

20.2 ያለ እርሱ ምንም ፍሬ ማፍራት እንደማንችል መገንዘብ፡- "እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፍ ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።" (ዮሐ. 15፡5)

20.3 ለፍሬያማ አገልግሎት እኛ በጌታ ውስጥ እርሱም በእኛ ውስጥ መሆኑ አስፈላጊ እንደ ሆነ ማስታወስ። (ዮሐ. 15፡5 ተመልከት)

20.4 መቶ እጥፍ ስናፈራ አብ በዚህ እንደሚከብር ማመን። (ዮሐ. 15፡16 ተመልከት።)

20.5 ይህ የሚቆይ ፍሬ እንጂ ጊዜያዊ ያለ መሆኑን ልብ ማለት።

20.6 ለውጤታማና ፍሬያማ አገልግሎታችን አብ በክርስቶስ ስም የምንጠይቀውን ሁሉ እንደሚሰጠን ማመን። (ዮሐ. 15፡16 ተመልከት።)

20.7 የአገልግሎታችን ፍሬ አንድ ቀን በእሳት እንደሚፈተን ያለ መርሳት። (1ቆሮ. 3፡10–15 ተመልከት።)

20.8 አገልግሎታችን እንደ ወርቅ፤ አልማዝና ብር ተፈትኖ ቢጸና ሽልማት እንዳለን ማወቅ። (1ቆሮ. 3፡8 ተመልከት።)

20.9 ለታይታ ሳይሆን በፍቅር እንድናገለግል መጠራታችንን ያለ መዘንጋት።

20.10 የምናገለግለው ጌታን መሆኑን ልብ ማለት፤ "ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት ከጌታ የርስት ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና፤ የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና።" (ቆላ. 3፡23–24) የመሳሰሉት ናቸው።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ሹመት ምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. የአገልግሎት ፍሬ ሲባል ምን ማለት ነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

3. የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን ዓይነት ፍሬ እንድናፈራ ነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

4፡ ምን ያህል ፍሬ እንድናፈራ ይጠበቅብናል?

- ♦
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦

## 21. ጥበብን ይሰጥሃል

"ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱም ይሰጠዋል።" (ያዕ. 1፡5)

"ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን።" (ኤፌ. 1፡8)

"ብቻ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ሕግ ትጠብቅ ዘንድ እግዚአብሔር ጥበብና ማስተዋልን ይስጥህ፤" (1ዜና 22፡12)

"ለተጠሩት ግን አይሁድ ቢሆኑ፤ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ፤ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው።" (1ቆሮ. 1፡24)

"ጌታም በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይሰጥሀ።" (2ጢሞ. 2፡7)

"ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም፤" (ቆላ. 1፡9)

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ጥበብ ምንድነው?

- ♦
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦

2. በእውቀትና በጥበብ መካከል ልዩነት አለ ብለህ ታስባለህ? ልዩነታቸውን ዘርዝር?

- ♦
- ♦

♦

♦

♦

## 22. ጌታ ለዘላለም አይለይህም

"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" (ማቴ. 28፡20)

"እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኗል፤ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።" (ማቴ. 1፣23)

ሁሉን የሚችል፤ በሁሉም ቦታ የሚገኝ፤ ሁሉንም የሚያውቅ የማይለወጥና በፍጹም ፍቅር የወደደን ጌታ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ነው። በመሆኑም፤

22.1 በእያንዳንዱ ሰከንድ ከእኛ ጋር ነው።

22.2 በየደቂቃው ከእኛ ጋር ነው።

22.3 በየዕለቱ ከእኛ ጋር ነው።

22.4 በየዓመቱ ከእኛ ጋር ነው።

22.5 ዕድሜያችንን በሙሉ ከእኛ ጋር ነው።

22.6 በሚመጡት ዘመናት እስከ ዘላለም ከእኛ ጋር ይሆናል።

22.7 ሁኔታዎች ሳያግዱት ሁልጊዜና በሁሉም ስፍራ ከእኛ ጋር ነው፤

◊ በተራራም — በመጥገብ

◊ በሸለቆም — በመራብ

◊ በገነትም — በመብዛት

◊ በበረሃም — በመጉደል

| | |
|---|---|
| ◊ በአገርም ውስጥ | በመከበር |
| ◊ ከአገርም ውጭ | በመዋረድ |
| ◊ በቤትም ውስጥ | በስደት ...ወዘተ. |

8. በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ከእኛ ጋር ይሆናል፤

| | |
|---|---|
| ◊ በብርታት ጊዜ | በሚመስለንም ጊዜ |
| ◊ በድካምም ጊዜ | በማይመስለንም ጊዜ |
| ◊ በጤንነትም ጊዜ | በሙላትም ጊዜ |
| ◊ በችግርም ጊዜ | በጉድለትም ጊዜ |
| ◊ ህልውናው በሚሰማንም ጊዜ ሆነ | በብቸኝነትም ጊዜ...ወዘተ። |
| ◊ በማይሰማን ጊዜ | |

ንጉሥ ዳዊት ይህን ስለ ተለማመደ ነው እንዲህ ያለው፦ "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ ወደ ሲኦልም ብወርድ አንተ በዚያ አለህ። እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፤ በዚያ እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ትይዘኛለች።" (መዝ. 138፡7-10)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር መገኘት ስንል ምን ማለታችን ነው?

◆ 
◆ 
◆ 
◆ 
◆ 

2. ጌታ ከእኛ ባለመለየቱ ምን ትርፍ እናገኛለን?

◆ 
◆ 
◆ 
◆ 

## 23. በዓለም ካለው ይልቅ በአንተ ያለው ይበልጣል

"ልጆች ሆይ፤ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፤ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና።" (1ዮሐ. 4፥4)

በዓለም ያለው ሁሉ የተፈጠረና ለክርስቶስ ጌትነት የሚንበረከክ ነው። በእኛ ውስጥና ከእኛ ጋር ያለው ግን ሁሉን የፈጠረ ሰማይ ዙፋኑ ምድርም የእግሩ መረገጫ የሆነች ታላቅና ድንቅ አምላክ ነው። "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ሰማይ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ሥፍራ ምንድር ነው?" (ኢሳ. 66፥1) ተወዳዳሪ የለውም!

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. "በዓለም ያለው" ሲል ምን ማለቱ ነው?

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________

2. በአንተ ውስጥስ ያለው ማን ነው?

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________

## 24. የክብር ንጉሥ ካህን ሆነሃል

"ለወደደን ከኃጢያታችንም በደሙ ላጠበን፤ መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገን ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን አሜን።" (ራእይ 1፥6)

የክህንነትን አገልግሎት የተለየ የሚያደርገው የተለየ የክህነት ልብስ ለብሶ በእግዚአብሔር ፊት ማገልገሉ ነው። እኛንም እግዚአብሔር የጽድቅን ካባ አልብሶን እንደ ካህናት በክብሩ ዙፋን ፊት ሆነን እንድናገለግለው መርጦናል።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የካህን አገልግሎት ምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. የካህን ሃላፊነትስ?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

3. የካህን ኑሮ መለያዎች ምንድን ናቸው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

4. የክህነትን አገልግሎት ከሕይወት ጋር አዛምደው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

## 25. ከክብር ወደ ክብር ትለወጣለህ

“እኛ ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።” (2ቆሮ. 3፡18) መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ በሙላት እየሠራ ቀን በቀን ከክብር ወደ ክብር ያሸጋግረናል።

### ስለ ቃሉ የተሰጡ ተስፋዎች

ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል ወደ ደህንነት ይመጣል። “እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤” (ኤፌ. 1፡13 (ሮሜ 10፡14–15 ተመልከት)። ክርስቲያን እምነቱን የሚያሳድገው በቃሉ ነው። “እንግዲህ እምነት ከመስማት ነው መስማትም ከእግዚአብሐር ቃል ነው።” (ሮሜ 10፡17) ሕይወቱንም የሚገነባውና የሚያሳድገው በቃሉ ነው። “ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ፤ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ።” (1ጴጥ. 2፡2–3) ሕይወቱንም የሚያነጻው በቃሉ ነው። “በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው።” (ዮሐ. 17፡17) ስለዚህ ከደህንነት ጀምሮ የእግዚአብሔር ቃል ለዕድገት፤ ለቅድስና ኑሮ እንዲሁም ለአገልግሎት ዝግጅት በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ነቢዩ ቃሉን መፈለግና ማንበብ እንዳለብን ይመክረናል፤ “በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም አፌ አዝዞአልና፤ መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልጀራውንም የሚያጣ የለም።” (ኢሳ. 34፡16) ሐዋርያው

ጳውሎስም የቃሉን ቅርበት ሲጽፍ እንዲህ ይላል፡- “በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፣ ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው።” (ሮሜ 10፡8) ለጢሞቴዎስ ለምን ቃሉን ማንበብና ማጥናት እንደሚገባው ሲመክረውም “የእግዚአብሔርም ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ

ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።" (2ጢሞ. 3፡16–17) ይለዋል። ከቁጥር 26–33 ያሉት የቃሉ ተስፋዎች ናቸው በጥንቃቄ እናጥናቸው።

## <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. ከክብር ወደ ክብር የመሸጋገር ምስጢሩ ምንድነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

2. የሚለወጠውስ ምናችን ነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

3. ከክብር ወደ ክብር ማሸጋገሩ የማን ሥራ ነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

4. የእኛ ኃላፊነት በሂደቱ ውስጥ ምን የሚሆን ይመስልሃል?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

# 26. በቃሉ ሙላት እንድትኖር ተሰጥቶሃል

"የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ በጥበብ ሁሉ እርስ በእርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ በጸጋውና በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።" (ቆላ. 3፡16)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. በቃሉ ሙላት ስንኖር የምናገኘው ጥቅም ምንድን ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. ቃሉን ባለማወቃችን ምክንያት በሕይወታችን ውስጥ የሚከሰቱት ችግሮች ምንድን ይመስሉሃል?

- 
- 
- 
- 
- 

## 27. የቃሉ ሰይፍ የተሰጠህ የጌታ ወታደር ነህ

"የመዳንን ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።" (ኤፌ. 6፡17)

"የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፤ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለያይ ድረስ ይወጋል፤ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፤" (ዕብ. 4፡12)

"ከአፌ የሚወጣው ቃል እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል የላኩትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።" (ኢሳ. 55፡11)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የሰይፍ አገልግሎቱ ምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. ቃሉ በሰይፍ የተመሰለው ለምን ይመስልሃል?

- 
- 
- 
- 
- 

3. የተሰጠንን የመንፈሳዊ ሰይፍ አጠቃቀም ባለማወቅ የሚከሰቱ ጉዳቶች ምንድን ናቸው ትላለህ?

- 
- 
- 
- 
- 

## 28. የቃሉ መዶሻ የተሰጠህ ግንበኛ ነህ

"በውኑ ቃሌ እንደ እሳት፤ ድንጋዩንም እንደሚያደቅ መዶሻ አይደለችምን? ይላል እግዚአብሔር።" (ኤር. 23፡29)

### <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. የመዶሻን አገልግሎት ከቃሉ ጋር አነጻጽር?

- 
- 
- 
- 
- 

2. የአናጢን ሥራ ከአገልግሎትህ ጋር አነጻጽር።

- 
- 
- 
- 
- 